1 አጎበርን በአግባቡ እና ሁል ጊዜ እንጠቀም

2 አጎበራችንን በየአራት ወሩ አጥበን ጥላ ሥር በማስጣት እንጠቀም

3 ትኩሳት፣ ራስ ምታትና የማንቀጥቀጥ ስሜት ካለን ፈጥነን ወደ ህክምና መስጫ እንሂድ

4 የታዘዘልንን መድሃኒት በአግባቡ ጨርሰን እንውሰድ

5 ቤታችንን የፀረ-ወባ ትንኝ ኬሚካል እናስረጭ

6 የተረጨውን ግድግዳ አንለስን ወይም በወረቀት አንለጥፍ

የዓለም የወባ ቀን

# የወባ መከላከያ ዘዴዎች



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Health

CDC USAID President's Malaria Initiative

JOHNS HOPKINS Center for Communication Programs

ROLL BACK MALARIA PARTNERSHIP

ወባን በጋራ ጨርሶ እናስወግድ

የዓለም የወባ ቀን



## 1 አጎበር መጠቀም

ሁሉም የቤተሰብ አባላት ለነፍሰ ጡሮች እና ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት ቅድሚያ በመስጠት ዘወትር ምሽት በፀረ-ወባ ኬሚካል በተነከረ አጎበር ውስጥ እንዲተኙ አድርጉ፡፡

በመኝታ ጊዜ የአጎበሩን የታችኛውን ጫፍ ከፍራሹ ስር መወሸቁን አረጋግጡ፡፡



## 2 አጎበርን ማጠብ

የአልጋ አጎበራችሁን በየአራት ወራቱ በልብስ ሳሙና አጠቡት፡፡ በጥላ ውስጥ በመስቀል ወይም በማስጣት እንዲደርቅ አድርጉት፡፡



## 3 ህክምና ማግኘት

በማንኛውም ጊዜ የቤተሰብ አባላት የትኩሳት ስሜት ሲኖራቸው በፍጥነት በአቅራቢያቸሁ ወደሚገኘው ጤና ተቋም ውሰዷቸው፡፡



## 4 መድሃኒት መውሰድ

የፀረ-ወባ መድሃኒትን በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ ወይም በህክምና ባለሞያ በታዘዘው መሰረት ሳያቋርጡ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

መድሃኒቱን ማቋረጥ ወይም ለሌላ ሰው ማካፈል የለበትም፡፡



## 5 የፀረ-ወባ ኬሚካል ማስረጨት

የፀረ-ወባ ኬሚካል በሚረጭባቸው ጊዜያት ኬሚካሉን ለሚረጩት ባለሞያዎች አስፈላጊውን ትብብር አድርጉ፡፡

በመኖሪያ አካባቢ የሚገኙ ውሃ የሚይዙ እና ጥቅም የማይሰጡ ቁሳቁሶችን፣ ረግራጋማ ቦታዎችን ማፅዳት፣ ማፋሰስ ወይም ማዳፈን ያስፈልጋል፡፡



## 6 ግድግዳውን አስመስሰን

የፀረ-ወባ ኬሚካል የተረጨውን ግድግዳ ለስድስት ወራት በአበትም ሆነ በጭቃ አትለቅልቁት፤ ወረቀትም አትለጥፉበት፡፡